# እርሻ ለወፍራም ጉርሻ!!

ከአርሶ አደሩ እርሻ እስከ እያንዳንዳችን የጓዳ ጉርሻ ድረስ ያለው የሰብል ልማት ተግባር ከአምራቹ ገበሬ ባለፈ የሁሉም ዜጋ ሀላፊነት ነው። አርሶ አደሩ በወቅቱ ሰብሉን አምርቶና በግብይት ሰንሰለት አልፎ በጓዳችን ተከሽኖ እስከ ጉርሻ ያለው ሂደት አብዛኛው በአርሶ አደሩ ጫንቃ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ከመሆን ተላቆ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ማበርከት እንዳለበት ጊዜው ያስገድዳል።

ዛሬ ያ ደጉ ዘመን አልፏል! ጫር ጫር አድርገው ለበተኑላት እፍኝ ጥሬ መሬትም እጥፍ ድርብ አደርጋ የምትመልስበት ወቅትም ላይመለስ አክትሟል። መሬት ወዘናዋ እየተሟጠጠ ድጋፍና እንክብካቤን ትሻለች፤ አጥግቦ ለሰጣት አትረፍርፋ ትመልሳለች። አልያ ግን መሬትም ወይ ፍንክች ማለት ከጀመረች ሰንባብታለች።

ይህን ደግሞ አርሶ አደሮች በውል ተረድተዋል፤ ያላቸውን የእርሻ መሬት በወቅቱ ከማረስና ከማለስለስ ባለፈ ወቅቱን ጠብቀው ከተፈጥሮ ማዳበሪያ(ኮምፖስት) ከማዘጋጀት በዘለለ ዳፕ፣ ዩሪያ፣ቦሮና የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን በመጠቀም ከመሬት የተሻለ ምርት ለማግኘት ዘወትር ይታትራሉ።

ዛሬም በምዕራብ ጎጃም ዞን ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች መሬታቸውን አርሰውና አለስልሰው የማደበሪያ እና ምርጥ ዘር ግብዓትን ለማግኘት ጥረት እያደረጉ አግኝተናቸዋል።

አርሶ አደር አሌ ቢሻው በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ወርቅምላ አጫደር ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። አርሶ አደሩ ሰሞኑን ከባድማቸው ተለይተው መሸንቲ እና ይነሳ ሶስቱ ቀበሌ መዋል ማደር ጀምረዋል። ለዚህ የዳረጋቸው ደግሞ ያላቸውን የእርሻ መሬት አርሰውና አለስልሰው ጨርሰዋልና ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለማግኘት ነበር።

በመሸንቲ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ያገኘኃቸው አርሶ አደር አሌ "ዘንድሮ ወቅቱ ጥሩ ነው፤ ዝናቡም ቀድሞ መጥቶልናል እኛም መሬታችንን አዘገጃጅተን የሚያስፈልገንን ግብዓት ለመግዛት ነው የመጣሁት ሲሉ ይገልፃሉ።

አርሶ አደሩ መንግስት ዘንድሮ የማዳበሪያ አቅርቦቱን በበቂ ሁኔታና በተቀላጠፈ መንገድ ነው ያቀረበልን! ዳፕም ዩሪያም በወቅቱ አግኝተናል በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን አሁን ትልቅ ፈተና የሆነብን በዚህ ወቅት የሚያስፈልገን የበቆሎ ምርጥ ዘር በፍፁም ልናገኝ አልቻልንምና እዚህ ከተማ ለከተማ ምርጥ ዘር ፍለጋ ስንታመስ እንውላለን" ሲሉም ይገልፃሉ።

እኛ የምንዘራው በቆሎና ዳጉሳ ነው። በቅድሚያ የምንዘራው ደግሞ በቆሎ ነው። የሚያስፈልገንም ሊሙ እና ቢኤች 540 የተሰኘ የበቆሎ ምርጥ ዘር ነበር ነገር ግን ምንም ማግኘት አልቻልንም" ሲሉ የሚገልፁት አርሶ አደር አሌ መንግስትም እንደ ማዳበሪያው የበቆሎውን ምርጥ ዘር ካላቀረበልን መሬታችንን ዳዋ ወርሶት መክረሙ ነው ሲሉም አርሶ አደሩ ጭንቅ ውስጥ እንዳም ያስረዳሉ።

"እኔ ሶስተኛ ቀኔን ይዣለሁ ባድማዬን ጥዬ መሸንቲና ይነሳ ምርጥ ዘር ፍለጋ የምንከራተተው" በማለት የሚገልፁት አርሶ አደር አሌ ግን ጠብ ያለ ነገር ማግኘት እንዳልቻሉ ተናግረዋል። በእኛ አካባቢ የሚዘራው በቆሎ እና ዳጉሳ ነው አሁን ግንቦት መጀመሪያ ላይ በቆሎአችንን ዘርተን ወደ ዳጉሳ እንገባ ነበር ነገር ግን ሊሙ እና ቢኤች 540 የተሰኘው የበቆሎ ምርጥ ዘር ባለማግኘታችን ባድማችንን ጥለን ከተማ ምርጥ ዘር ፍለጋ እንከራተታለን በማለት በከፋ እንግልት ላይ እንዳሉም ይገልፃሉ።

አርሶ አደሩ እንደሚገልፁትም የተመረጠ የአምና ዘር በቤታቸው ቢኖርም አበጣጥረን ብንጥለው በአግባቡ አያፈራም ስለዚህ የከረመውን ዘር አልጠቀመውም ነገር ግን በሌላ ወረዳ ሜጫም ድረስ ሄጄ ፈልጌ በውድ ዋጋም ቢሆን ገዝቼ ለመጠቀም ወስኛለሁ" ሲሉም ያስረዳሉ።

አርሶ አደር አሌ ሁለት ሄክታር መሬት አላቸው አንዱ የበቆሎ አንዱ የዳጉሳ ሁለቱንም አዘጋጅተው ቅድሚያ የበቆሎ ዘርን ለመጣል ቢጥሩም የምርጥ ዘር እጥት ቆልፎ ይዞአቸው ከተማ ለከተማ ያንከራትታቸዋል። አቶ አሌም "መንግስት ምናለ እንደ ማዳበሪያው ምርጥ ዘሩንም በወቅቱ ቢያቀርብልን" ሲሉም ተማፅኖ ያቀርባሉ። ያለ ምርጥ ዘር ቦዘኑን ማዳበሪያ ምንስ እናደርገዋለን ሲሉም መልስ ያጡለትን ጥያቄ ለራሳቸው ያቀርባሉ።

ሌላው በዘንዘልማ ደብረፅዮን ህብረት ስራ ማህበራት ያገኘናቸው አርሶ አደር አባይ አለልኝ ይባላሉ። እኝህ አርሶ አደር እንደሚገልፁትም "እኔ ሌላ ትምህርት የለኝም ዕውቀቴ እርሻ ብቻ ነው ይህንንም በደንብ አድርጌ አርሼና አለስልሼ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያን በመጠባባቅ ላይ ነኝ" በማለት ያስረዳሉ።

አሁን በቆሎን ለመጣል ዝግጅቴን ጨርሻለሁ ነገር ግን የምጥለው የበቆሎ ምርጥ ዘር ጭራሽ ማግኘት አልቻልኩም፤ ዳፕም በበቂ ልክ አልደረሰኝም ሲሉ ያስረዳሉ። በተለይ የምርጥ ዘር ጉዳይ አርሶ አደሩን በሙሉ ጭንቀት ውስጥ እንደከተተውም በምሬት ይናገራሉ።

የአምናውን ዘር አበጣጥረን ብንጠቀም ቁመት እንጅ ፍሬ እንደማያፈራ ካለፈ ተሞክሯችን አይተነዋል የሚሉት አኝህ አርሶ አደር "መንግስት ተመራምሮ ከአመጣው ሊሙ እና ቢኤች 540 ምርጥ ዘር ውጭ መሬቱ በአግባቡ የሚለማ ወይም ፍሬ የሚሰጥ አይደለም" ሲሉም ይናገራሉ።

መንግስት እንዴት ምርጥ ዘር ሳያቀርብ ማደበሪያው ብቻ ምን ያደርግልናል ሲሉ የሚጠይቁት አርሶ አደሮች በውድ ዋጋም ቢሆን ሌላ ወረዳ ሄደው ለመግዛት እንዳሰቡም ያስረዳሉ። መንግስት አርሶ አደሩን በምርጥ ዘር በኩል እያገዘው አይደለም! ከውጭ የሚመጣውን ማዳበሪያ በወቅቱ መንግስት ማቅረብ ከቻለ እንዴት የብዜት ማዕከል በክልላችን እያሉ በምርጥ ዘር

ልንጉላላና ልንቸር ቻልን? ሲሉም ብርቱ ጥያቄ መሳይ ቅሬታቸውን ያቀርባሉ።
በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት የስራ ሂደት መሪ ወ/ሮ ሙሉ አደራው በወረዳው 110 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ ለማቅረብ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ 63 ሺ 167 ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ህብረት ስራ ማህበራት መግባቱን አስረድተዋል። ከዚህ ከገባው ማዳበሪያም 58 ሺ 970 ኩንታሉ ለአርሶ አደሮች መሰራጨቱንም ገልፀዋል።
ወይዘሮ ሙሉ የምርጥ ዘርን አቅርቦት በተመለከተ ሲገልፁ በእቅድ ቢኤች 540፣ ቢኤች 660፣ 661 እና ሊሙ የበቆሎ ምርጥ ዘር 5 ሺ 250 ኩንታል ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ የታቀደ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ለአርሶ አደሮች የተሰራጨው ግን 407.5 ኩንታል ብቻ እንደሆነ አስረድተዋል። ይህ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ አሁን ላይ የአርሶ አደሩ ጥያቄ እየበረታ እንደመጣ አስረድተዋል።
በተለይ የቢኤች 540 እና ሊሙ የበቆሎ ምርጥ ዘር ለወረዳው አርሶአደሮች እጅግ ተስማሚና ምርታማ ስለሆነ ተፈላጊ እንደሆነም ወይዘሮ ሙሉ ተናግረዋል። ይሁንንና በአርሶ አደሩ ፍላጎት ልክ ምርጥ ዘሩን ማቅረብ እንዳልተቻለና ጽ/ቤታቸውም መፍትሄ ለማፈላለግ እየሞከረ እንደሆነ ገልፀዋል።
በአሁኑ ጊዜ ወረዳው የአርሶ አደሮችን የበቆሎ ምርጥ ዘር ወቅታዊ ጥያቄ ለማስተናገድም አስከ ኦሮሚያ ክልል ድረስ ደብዳቤ ተፃፅፎ የአርሶ አደሮች ፍላጎት የሆነውን ምርጥ ዘር ለማስመጣት ጥረት እያደረገ እንደሆነም ገልፀዋል፤ ሂደት መሪዋ።
አቶ ሙሉቀን ገድፍ በመርከብ ዩኒየን ድርጅት ውስጥ የዘር ብዜት ባለሙያ ነበሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ። እንደ አቶ ሙሉቀን አስተያየት መርከብ ዩኒየን ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ የዘር ብዜትን በማዘጋጀት ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት እንደ ሆነ ይገልፃሉ።ይሁንና ዩኒየኑ በየዓመቱ ከ 50 እስከ 100 ሄክታር መሬት ላይ የዘር ብዜት የማከናወን አቅድ ቢኖረውም የመሬት ችግር ስላለ በአግባቡ እንዳላከናወነም አስረድተዋል።
በባለፈው ዓመት በሰሜን አቸፈር ወረዳ 37.5 ሄክታር መሬት ላይ የዘር ብዜት በማከናወን ለአርሶአደሩ 685 ኩንታል ቢኤች 540 የበቆሎ ምርጥ ዘርን ለአርሶ አደሮች ማሰራጨታቸውን ያስታውሳሉ። "ዘንድሮ ግን የምርጥ ዘር መስራች ዘር ከኦሮሚያ ቢመጣም የብዜት መሬት ስላላገኘ የበቆሎ ምርጥ ዘር ቤዜት አላከናወንም" ሲሉም ይገልፃሉ።
በአጠቃላይ እንደ አቶ ሙሉቀን አስተያየት በክልሉ ከአስር በላይ የምርጥ ዘር የብዜት ማዕከላት አሉ፤ የሰው ሀይል እጥረትም ስለዚህ ክልሉ ብዜት ስራ ላይ ያለውን የመሬት ችግር በመቅረፍ በየጊዜው የሚፈጠረውን የምርጥ ዘር እጥረት መቅረፍ ይቻላል ሲሉም ሀሳባቸውን ሰጥተዋል።
በመርከብ ዩኒየን የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት የስራ ክፍል ሀላፊ የሆኑት አቶ ተመስገን አበበ በበኩላቸው በአሁኑ ጊዜ ራሳቸው የዘር ብዜት ማዕከላት ያባዙትን ዘር ለአርሶአደሮች የሚያደርሱበት ስርዓት እንዳለ ይገልፃሉ።
መርከብ ዩኒየን በምርጥ ዘር ብዜት እንዳላከናወነ የሚገልፁት አቶ ተመስገን ነገር ግን ከአዲስ አበባ በማስመጣት 1 ሺ 990 ኩንታል ሊሙ የበቆሎ ምርጥ ዘርን ለአርሶ አደሮች ማከፋፈላቸውን አስረድተዋል።
የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ሀላፊ አቶ ተስፋሁን መንግስቴ በበኩላቸው በክልሉ ምንም ዓይነት የአፈር የማዳበሪያ እጥረት የለም እንደውም ትርፍ በመካዝንም ሊኖር እንደሚችል ይገልፃሉ።
አሁን ላይ ከከረመው ባለፈ 3.7 ሚሊየን ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ክልል ገብቷል ያሉት ምክትል ቢሮ ሀላፊው ቀሪውም በመጓጓዝ ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል።
ምርጥ ዘር ግን በተለይ የበቆሎ ምርጥ ዘር በአንዳንድ አካባቢዎች ፍላጎትና አቅርቦት ያለ መጣጣም ችግር እንዳለም ተናግረዋል። በተለይ "ሊሙ" የተሰኘው የበቆሎ ምርጥ ዘር በክልሉ እጥረት እንዳለም አንስተዋል።
ነገር ግን አርሶ አደሮች እሱን የሚተካ ሌሎች ምርጥ ዘሮች አሉና እነሱን በመጠቀም ማሳቸው ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።
91 ሺ 154 ኩንታል ምርጥ ዘር ወደ ክልሉ መግባቱን የሚገልፁት ምክትል ቢሮ ሃላፊው ከዚህ ከገባው ውስጥም 70 ሺ 714 ኩንታል ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሮች መሰራጨቱንም አስታውቀዋል።
በአጠቃላይ በክልሉ የምርጥ ዘርም የሆነ የአፈር ማዳበሪያ እጥረት እንደሌለ የሚገልፁት አቶ ተስፋሁን ችግሩ ያለው አርሶ አደሩ ሊሙ እና ቢኤች 540 ብቻ ነው የምጠቀመው የሚልከሆነ ብቻ ነው ብለዋል።
በክልሉ ሊሙ እና ቢኤች 540 የበቆሎ ምርጥ ዘር እጥረት እንዳለ የሚገልፁት ቢሮ ሀላፊው ነገር ግን ይህንን የሚተካ 546 እና ሌሎች ምርጥ ዘሮች በበቂ ሁኔታ መኖራቸውን አስታውቀዋል።
በቀጣይ በዘላቂነት የምርጥ ዘር እጥረትን ለመቅረፍ ለዘር ብዜት ማዕከላት ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የጠቆሙት ሀላፊው ጠቅመዋል። የእኛ ክልል የብዜት ማዕከላት የራሳቸው የብዜት መሬት የላቸውም በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ነው የሚያባዙት ያሉት አቶ ተስፋሁን የራሳቸው መሬት አጊንተው በስፋት እንዲሰሩም የክልሉ መንግስት ድጋፍ እንደሚያደርግም አስረድተዋል።